**ኢትዮሚዲያ**

**ርእሰ አንቀፅ**

# የሞት ቅጣት በጠማ ፍርድ ቤት

**ትርጉም በኦላና ኦብሴ**

ፍትህ አጅግ ተፈዘባት! መለስ መንግስቱ ኃይለማርያምንና አበሮቹን በስእብና ላይ ባደረሱት ታላቅ ወንጀል እንዲሰቀሉ መፍረድ። አስቲ አስቡት አዶልፍ ሂትለር ቢኒቶ ሞሶሎኒ በኢትዮጵያውያን ላይ በፈጸመው የጦር ወንጀል የሞት በቃ ሲፈርድ። ማሰሮ ጀበናን ጠቀረች ብላ ስትሳለቅ ይታያችሁ ።



**አምባገነኑ መንግስቱና ቅጥረኛው መለስ**

**የሕዝቡን ሰብእና ከ1966-1983 የገፈፈውና በህይወት የሚገኘው ጨካኙ አባገነን መንግስቱ በግራ በኩል እንደዚሁም የሕዝቡናና የሀገሪቱን ሉአላዊነት በመርገጥ ላይ የሚገኘው ርህራህ የለሹ ቅጥረኛ መለስ ዜናዊ በቀኝ በኩል**

የመለስ ማህበረተኞች ቃል አቀባይ ዮሴፍ ኪሮስ ባለፈው ሳምንት እንዳስታወቀው መንግስቱና 18 የቀድሞ ባለስልጣን ተከሳሾች "በሰው ልጆች ላይ በፈፀሙት ታላቅ ወንጀል ምክንያት በሞት እንዲቀጡ ተፈርዶባቸዋል።" የመንግስቱ "የሞት ፍርድ" መነሻው 1969/1970 ያካሄደው የቀይ ሽብር ዘመቻና በወቅቱም በሰብአዊ መብት ታዛቢዎች በአፍሪካ ታሪክ ውስጥ አቻ የማይገኝለት በመንግስት የተቀነባበረ ጭፍጨፋ" የተባለለት ወንጀል ነው። የመለስ አጫፋሪ አጭበርባሪው ፍርደ ገምድል ደስታ ገብሩ የሞት ፍርዱን ውሳኔ ሲገልፅ መንግስቱና የወንጀል ተባባሪዎቹ በሺህ የሚቆጠሩ ንፁሃን ዜጎችን ደብድበዋል ረሽነዋል ይህም በኢትዮጵያ ህግ እንደ ዘር ማጥፋት ይታያል ብሏል።

## ማሰሮ ጀበናን ጠቆርሽ አለቻት

በኢትዮጵያ ዛሬም ከ1969/1970 ዓ. ም የተለወጠ ምንም አዲስ ነገር የለም። በሺዎች በሚቆጠሩ ንፁሃን ዜጎች ላይ ዛሬም ድብደባና ግድያ ይካሄዳል። ድርጊቱ ከመቸውም በላይ እየተስፋፋ ነው። የሰብአዊ መብት ታዛቢዎች ዛሬም በ2000 ዓ.ም በመለስ አገዛዝ ላይ የሚሰጡት አስተያየት ይኸው ነው። የኢትዮጵያ መንግስት በሃገር ውስጥና በጎረቤት ሶማሊያ ከፍተኛ የመብት ረገጣ ያደርጋል ይላል ዘገባው። በምስራቅ ሶማሌ እያደገ የመጣውን አመጽ ለመቆጣጠር የመንግስት ሃይሎች ባደርጉት ዘመቻ አስገድዶ በመድፈር፣ በመደብደብና መንደሮችን በማቃጠል በህዝብ ላይ ከባድ ወንጀል ፈጽመዋል……በመለስ የሚታዘዘው የወያኔ የጦር ኃይል የአለም አቀፍ ህጎችን በመጣስ በየካቲትና በመጋቢት 1999 ዓ.ም የሶማሊያ ዋና ከተማን ሞቅዲሾን በመድፍና በሮኬት በመደብደብ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሲቪሎችን ገድሎ 400,000 የሚገመቱ ሰዎችን ከመኖሪያቸው አፈናቅሏል። ችግሩ በደረሰባቸው አምስት የሶማሌ ክልል ዞኖች የወያኔ የጦር ኃይል መንደሮችን በማጋየት፣ በአደባባይ ሰዎችን በመረሸን፣ ሴቶችንና ለአቅመአዳም ያልደረሱ ልጃገረዶችን በመድፈር፣ ከህግ ውጪ በማሰርና በመግረፍ አንዳንዴም በጦር ካምፕ በቁጥጥር ስር ያሉ እስረኞችን በመግደልና በሺዎች የሚቆጠሩ አካባቢያቸውን ለቀው እንዲሰደዱ በማስገደድ በነዋሪው ላይ የበቀል እርምጃ ወስደዋል። በህዝብ ብዛቱ በኢትዮጵያ ተቀዳሚውን ስፍራ በያዘው በኦሮሚያም የመንግስት ባለስልጣናት ለረጂም ጊዜ የቆየውን የኦሮሞዎች አመፅ እያሳበቡ ተቃዋሚዎችን ያስራሉ፣ ያዋክባሉ፣ የአካል ጉዳትም ያደርሱባቸዋል። ተማሪዎች የችግሩ ሰለባዎች ናቸው። የመንግስትን ፓርቲ አልደግፍ ያሉ ገበሬዎችም አገዛዙ ሙሉ በሙሉ የሚቆጣጠራቸውን እንደ ማዳበሪያና ሌሎች ለእርሻ የሚጠቅሙ እርዳታዎች ይነፍጉዋቸዋል።የሰብአዊ መብት ታዛቢዎች በ1995 ዓ.ም በአኙዋክ ብሄረሰብ ላይ የደረሰውን ጭፍጨፋ አስመልክቶ የሚከተለውን ዘግበዋል። ግድያው በሚካሄድበት ወቅት የኢትዮጵያ

መከላከያ አካል የሆነው 43ኛ ክ/ጦር አባላት አብዛኛው በጋምቤላ ከተማ ውስጥ ነበሩ። ከመቶ በላይ የሚሆኑ የጦሩ አባላትም በግድያው ላይ በቀጥታ ተካፍለዋል። ትኩረታቸው በአኙዋክ ጎልማሶች ላይ ቢሆንም የጥፋቱ ሰለባዎች እነሱ ብቻ አልነበሩም። ወታደሮች በርካታ የአኙዋክ ሴቶችን ደፍረዋል፣ ከአራት መቶ በላይ የአኙዋኮች መኖሪያ ቤቶች በእሳት ጋይተዋል። በርካታ ሲቪል አኙዋኮችም ወደ ጫካ ሸሽተዋል ወይም በአካባቢው ባሉ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ቅጥር ግቢ ተጠልለዋል። ይህ ሲሆን የጋምቤላ ከተማ የጦር አዛዥ ሻለቃ ፀጋዬ በየነ እዚያው ጋምቤላ ከተማ ውስጥ ነበረ። ግድያውንና ጥፋቱን ከማስቆም ይልቅ የግድያው ተባባሪ ሆኖ ተገኝቷል።

በመንግስቱ ላይ የሞት በቃ ለፈረደው የአቶ መለስ ፍርድቤትና ለአጋፋሪዎቹ የ2000ዓ.ም የሰብአዊ መብት ዘገባ እንዲህ ይላል። “ፍ/ቤቶች በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ከመንግስት ጣልቃ ገብነት ነፃ በሆነ ሂደት መስራት አልቻሉም። ለምሳሌ በሀገር ክህደት ክስ ለመፍረድ የተሰየመው ዳኛው ለተከሳሹ መብት፣ ለህግ ደንብና ስርአቶች መከበር ደንታ ቢስ ነው። በእስረኞች ላይ በጠባቂዎች የሚደርሱ በደሎችና አቤቱታዎች ችላ ተብለዋል። አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር ባጠቃላይ ፍ/ቤቶች ፖሊስ በተከሳሾች ላይ መረጃዎችን እንዲያፈላልግ ጊዜ ይሰጣሉ። በዚህ ጊዜ ተከሳሾች እስር ቤት ይቆያሉ። በዋስ አይፍቱም።”

“በ1998 ዓ.ም መለስ እራሱ ያቋቋመው የ1997 ዓ.ም ምርጫ ጋር ተያይዞ የደረሰውን እልቂት እንዲያጣራ ያዋቀረው የመርማሪ ኮሚሽን 1,300 ምስክሮችን አዳምጦ 16,990 መረጃዎችን ከመረመረ በሁዋላ የመለስ አምባገነን መንግስት 193 ያልታጠቁ ሰላማዊ ሰልፈኞችን ገድሎ ሌሎች 760 አቁስሏል” የመርማሪ ኮሚሽኑ ሊቀመንበር ዳኛ ፍሬህይወት ሳሙኤል እንደገለጹት “ብዙዎች የተገደሉት ያለምንም ምክንያት በመደዳ ነው። ሽማግሌዎች በቤታቸው እንደተቀመጡ ህጻናትም እግቢያቸው ውስጥ ሲጫወቱ ነው የተገድሉት።”ብለዋል

## ፍትህ ዘገየ፣ በግፍ ለተገደሉት ንፁሃን ፍትህ ተከለከለ

መለስ የሃያኛውን መእተዓመት አጋማሽ ታላቅ ወንጀለኛ “ለፍርድ” ለማቅረብ 17 አመት ፈጀበት። መለስ እንደዘበት መንግስቱ ባደረሰው ወንጀል ከተጠያቂነት እንዲያመልጥ እንደገና አግዞታል። ክሱን ውድቅ ለማድረግ መንግስቱ ብዙ አሳማኝ መከራከርያ ነጥቦችን ማቅረብ ይችላል።

1) ከሳሾቹ እራሳቸው ወንጀለኞች ስለሆኑ ለዳኝነት የሚያበቃ የሕግና የህሊናም ብቃት የላቸውም። (በሌላ አነጋገር ልበ ድንጋይ ወንጀለኞች ሌላ ልበ ድንጋይ ወንጀለኞችን ሊዳኙና ሊፈርዱባቸው አይችሉም።)

2) በእኔ ላይ የፈረዱት ሁሉ እኔ የተወነጀልኩበትን ተመሳሳይ ወንጀል እየፈፀሙ ስለሆነ ተመሳሳይ ፍርድ በእነሱም ይፈረድ ብሎ ሊሟገት ይችላል።

3) የውሳኔው 17 አመት መዘግየት ፍርዱ ፖለቲካዊ ጫና እንዳለበት ያመለክታል። በምንም አይነት በማንኛውም ህጋዊ ነኝ ባይ የህግ ተቋም አንድ ሰው ከ17 አመት በህዋላ ሊዳኝ አይችልም። እንዲያውም በአቶ መለስ ህገ መንግስት በአንቀፅ 20 “ ተከሳሽ ክሱ ያለመዘግየት ለፍርድ ቤት በይፋ መቅረብ አለበት” የሚለውን የተከሳሽ መብት ተነፍጎኛል በማለት መለስን ሊያዋርደው ይችላል። ነገር ግን “ፍትህን” ለማግኘት 17 አመት የፈጀ ዳኝነት እንከኑ የወሰደው ጊዜ ብቻ ነው

ተብሎ አይታለፍም። 17 አመት የወሰደ ፍትህ የዘገየ ፍትህ ሳይሆን በፍትህ ላይ ማላገጥ ማሾፍ ህግን መናቅና የመንግስቱ ወንጀሎች ሰለባ የሆኑትን ንጹሃን ወገኖች ፍርድ መከልከል ነው።

## መንግስቱ ክሱንም ፍርዱንም ከእራሱ ህሊና ፍ/ቤት ያገኘዋል

መንግስቱና ግብረአበሮቹ በትክክለኛ ለፍትህ በቆመ ፍ/ቤት አንደማንኛውም ሰው ቀርበው ጥፋታቸው መረጋገጥ አለበት። ደረጃውን ባልጠበቀ ሁኔታ በእነዚህ እኩይ አውሬ ወንጀለኞች ላይ ብቃት በሌለው፣ በሙስና በነቀዘ ዝርክርክ የጠጣ ፍ/ቤት ፍርድ መፍረድ ማለት ጥፋተኝነታቸውን የማያቁርጥ ጥርጣሬ ውስጥ ይከተዋል።
ምንም እንኩዋን መንግስቱና ግብረአበሮቹ በቀይ ሽብር ብቻ ሳይሆን ባጠቃላይ በደርግ ዘመን ቁጥር ስፍር የለሽ ወንጀል መፈፀማቸውንና ወንጀለኝነታቸውንም ብናምንም በህግ ላይ ያለን እምነት ደግሞ እጅግ የፀና ነው። ፍትህ ገና ስናስባቸው የሚያቅለሸልሹንን መንግስቱንና ደም የተጠሙ ባልደርቦቹን ከሃቀኛ ፍ/ቤት ቀርበው እያንዳንዱ ጥፋታቸው ለጥፋተኝነታቸው ማስረጃነት ብቻ ሳይሆን ጨቋኝ አስተዳደራቸው በሃገሪቱና በህዝቦቿ ላይ ያደረሰውን መከራና ስቃይ ለታሪክና ለመጪው ትውልድ መማርያ እንዲያገለግልም ጭምር በማስረጃነት ለቅሞና መዝግቦ መያዝን ይጠይቃል።

ግልፅነት በጎደለው ለፍትህ ባልቆመ በአቶ መለስ የጠጣ ፍ/ቤት ፍርድ የተነሳ እነዚህ ልባቸውንና በራቸውን ቆልፈው ከሰው እርቀው ያሉ ወንጀለኞች ፍርዳቸውን እስከወዲያኛውም እንዳያገኙ ረድቷቸዋል። ተስፋችን ግን አልሞተም። መንግስቱ ከሃራሬ ወጣ ብሎ በሚገኘው ልቅልቅ ቪላው ውስጥ ቁጭ ብሎ እለት በእለት የገረፋቸውንና የገደላቸው ንፁሃን ህሊናውን ሲሞግቱት ይውላሉ ብለን እናምናለን። ቢያንስ ቢያንስ እራሳችንን ለማጽናናት ያህል መንግስቱ በዚያ በተንቆጠቆጠ ሰፊ ቪላ ውስጥ ብቸኛ የቁም እስረኛ ነው ብለን እናምናለን። በህሊና መስታወቱ ወደ ሁዋላ እያየ ጨካኝ አውሬነቱን እለት በእለት ያስባል። መለስና መንግስቱ አንድ መዘንጋት የሌለባቸው ጉዳይ ቢኖር “የፍትህ ባቡር ብዙውን ጊዜ ቢዘገይም እንኩዋን ለእነሱ መሰል ጭራቆች ባልታሰበበት ሰአት ከች ማለቱ አይቀሬ ነው። የዛሬው መለስ ማለት የጥንቱ መንግስቱ ማለት ነው።”

## መለስና መንግስቱ ተግባራቸው አንድ አይነት ነው።

መንግስቱና መለስ ባቄላና ፍልፋዩ አንደማለት ናቸው። ጉልቻ ቢቀያየር ወጥ አያጣፍጥም። የሁለቱም መንትያ ጭራቆች የንጹሃንን ደም ለማፍሰስ ያላቸው የደም ጥማትና የጭካኔያቸው መጠን ከአውሬነት ባህሪይ የከፋ ነው። በ17 አመት የመንግስቱ የጭካኔ አስተዳደር በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ተጨፍጭፈዋል። ሀገሪቱ በሙስና፣ በጠረኝነትና በኢኮኖሚ ውድቀት ትሰቃይ ነበር። የመንግስቱ አስከፊ አስተዳደር ለኢትዮጵያ የተወላት ቅርስና ዝና ቢኖር አገሪቱ የአለም የረሃብ አርማ፣ሙሰኞች የሚብነሸነሹባት፣ ዜጎች መብታቸው በጅምላ የሚጣስበት የመከራ ምድር እንደሆነች ነው ለአለም ያስተዋወቃት። የመለስ አስከፊ አስተዳደር ከ17 አመት አስተዳደር በህዋላ ምን የተለየ ነገር ሰራ? ነገሮች በተቀያየሩ ቁጥር ተመሳሳይነታቸው ይበልጥ እየጎላ ይመጣል እንደሚባለው ነው።

## እንዲህ ተብሎም ተፅፏል

*መጸሀፍ ቅዱስ እርስ በእርሳቸው ለሚፈራረዱ ግብዞችና ክፉዎች ዘመን የማይሽረው ምልክት አለው። በማቲዎስ ወንጌል ምእራፍ 7 ክቁጥር 1-5*

*እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈርድባችኋልና*
*በምትሰፍሩበትም መስፈርያ ይሰፈርባችኋል*
*በወንድምህ አይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ በአይንህ ግን ያለውን ምሶሶ ስለምን አትመለከትም? ወይንም ወንድምህን ከአይንህ ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ እንዴትስ ትለዋለህ? እነሆም በአይንህ ምሶሶ አለ። አንተ ግብዝ አስቀድመህ ከአይንህ ምሶሶውን አውጣ ከዚያም በህዋላ ከወንድምህ አይን ጉድፉን ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ።*

*መለስ! መጀመርያ በአይንህ ውስጥ የተጋደመውን ግንድ አውጣ ከዚያም የወንድምህ የመንግስቱን ጉድፍ ለማውጣት በደንብ ይታይሃል።*

*በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም!*